**አዋጅ ቁጥር …../2014**

**ብሔራዊ የክፍያ ሥርዓት (ማሻሻያ) አዋጅ**

በብሔራዊ የክፍያ ሥርዓት ዉስጥ የተደረጉ ለዉጦችን፣ እድገቶችና መሻሻሎችን ታሳቢ በማድረግ የብሔራዊ የክፍያ ስርዓት አዋጅ ቁጥር 718/2003ን ማሻሻል አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገመንግሥት አንቀፅ 55 /1/ መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

1. **<u>አጭር ርዕስ</u>**

ይህ አዋጅ "**የብሔራዊ የክፍያ ሥርዓት (ማሻሻያ) አዋጅ ቁጥር** …../2014" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

<u>2. ማሻሻያ</u>

የብሔራዊ የክፍያ ስርዓት አዋጅ ቁጥር 718/2003 እንደሚከተለው ተሻሽሏል፤

1/ የአዋጁ አንቀጽ 2 ንዑስ—አንቀጽ (4)፣(12)፣(18) እና (20) ተሰርዞ በሚከተለዉ አዲስ ንዕስ፡አንቀጽ (4)፣(12)፣(18) እና (20) ተተክቷል፤

"4/ የመንግስት ሰነደ ሙዓለ-ንዋይ ማዕከላዊ ግምጃ ቤት" ማለት ፡

ሀ/ የመንግስት ሰነደ ሙዓለ ነዋዮች ወጥነት ባለዉ መልኩ የሚከማቹበት ወይም ወደ ኤሌክትሮኒክ ይዘት ተቀይረዉ የሚቀመጡበት ወይም ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች በመንግስት የሚመዘገቡበት ሆኖ እነዚህ ሰነደ ሙዓለ ነዋዮችን በተመለከተ የሚደረግ ግብይት ሰነዶቹን በአካል ማረካከብ ሳያስፈልግ የሰነዶቹ መተሳሰቢያ መዝገብ ላይ ብቻ በሚደረግ ወጪና ገቢ ለማስተላለፍ የሚያስችል ሥርዓት ነዉ።

ለ/ በመንግስት ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ግብይት ሂደት ወቅት የሰነዶች ሙዓለ ንዋዮችን ምዝገባ፣ ክፍያ ማጣራት፣ ርክክብ እና ማወራረድ ያለ አካላዊ ቅብብል ለማከናወን የሚያስችል ወይም ግብይቱን የሚያሳልጥ ዘዴ ወይም ስርዓት፤ እና ሌሎች ተያያዥ የሆኑ አገልግሎቶችን የሚሰጥ ስርዓትን ነዉ።

"12/"የፋይናንስ ተቋም" ማለት ባንክ፣ አነስተኛ የፋይናንስ ተቋም፣ የመድን ሰጪ ኩባንያ፣ የጠለፋ መድን ሰጪ፣ የክፍያ መፈጸሚያ ሰነድ አዉጪ፣ የክፍያ ስርዓት ኦፕሬተር የሐዋላ ድርጅት፣ የፖስታ ቁጠባ፣ ወይም በብሔራዊ ባንክ የሚወሰን ሌላ ተመሳሳይ ተቋም ነው፣"

18/"ኦፕሬተር" ማለት ብሔራዊ ባንክ፣ የፋይናንስ ተቋም፣ ወይም የክፍያ ትእዛዝን ወይም የመንግስት የዋስትና ሰነዶችን የሚያስተላልፍ፣ የሚያቻችል፣የሚያጣራ፣ የተጣራ የመጨረሻ ተከፋይ ሂሳብን የሚወስን

እና የሚያወራርድ ስርዓትን እንዲያቋቁምና እንዲሰራ ብሔራዊ ባንክ ፈቃድ ወይም ይሁንታ የሰጠው ሌላ ማንኛውም ኩባንያ ነው፤”

20/“የክፍያ መፈፀሚያ ሰነድ” ማለት አንድ ሰው የኢትዮጵያን ብር በሚስተካከል ገንዘብ ለሚከፍለው ክፍያ በልዋጭ የሚሰጠው ሰነድ ሲሆን ገንዘብ፣ ዕቃ ወይም አገልግሎት እንዲያገኝ ወይም ክፍያ እንዲፈፅም የሚያስችለው ግዙፍነት ያለውም ሆነ የሌለው ማናቸውም የኤሌትሮኒክ ገንዘብንና፣ ካርድን የሚጨምር ነዉ፤””

2 / ከአዋጁ ከአንቀጽ 2 ንዕስ፦አንቀጽ (28) ቀጥሎ የሚከተሉት አዲስ ንዑስ አንቀጾች (29)፣(30)፣(31)፣(32)፣(33) እና (34) ተጨምረዉ ነባሩ ንዕስ፦ አንቀጽ (29) ንዑስ - አንቀጽ (35) ሆኖ ተሸጋሽጓል፣

“29/"የውጭ አገር ገንዘብ" ማለት ከኢትዮጵያ ገንዘብ በስተቀር ከኢትዮጵያ ውጭ በማናቸዉም ሃገር ሕጋዊ ገንዘብ የሆነና በኢትዮጵያ ውስጥ ለሚደረግ ክፍያ ተቀባይነት እንዳለው ብሔራዊ ባንክ ያሳወቀው ማናቸዉም ገንዘብ ነው፤”

30/ “ኩባንያ” ማለት በኢትዮጵያ የንግድ ሕግ የተገለጸው የአክሲዮን ማህበር ሲሆን በኢትዮጵያ ሕግ መሠረት የተመዘገበና ዋና ጽሕፈት ቤቱ በኢትዮጵያ ውስጥ የሆነ ነው።

31/ “ኤሌክትሮኒክ ገንዘብ” ማለት አውጪው የሚገደድበት በኤሌክትሮኒክ መሳሪያ ወይም በሌላ የክፍያ መፈጸሚያ መሳሪያ ዉስጥ በኤሌክተሮኒክ ዘዴ የተከማቸ ፣ ከኢትዮጵያ ብር ጋር እኩል በሆነ መልኩ የሚፈጠር፣ ከአዉጪዉ ዉጪ ባሉት አካላት ለክፍያ ተቀባይነት ያለዉ፣ የክፍያ መፈጸሚያ የሆነ እና ወደ ጥሬ ገንዘብ መለወጥ የሚችል የገንዘብ እሴት ነዉ።

32/“የውጭ አገር ዜጋ ማለት“ የኢትዮጵያ ዜጋ ያልሆነ ሰው ነው።

33/“ተቀጥላ” ማለት በኢትዮጵያ የንግድ ሕግ የተሰጠዉን ትርጓሜ የያዘ ሆኖ በኢትዮጵያ ሕግ መሠረት የተመዘገበና ዋና ጽሕፈት ቤቱ በኢትዮጵያ ውስጥ የሆነ በቴሌኮም ኩባኒያ፣ በክፍያ ሰነደ አዉጪ ወይም በክፍያ ስርዓት ኦፕሬተር ቁጥጥር ስር ያለ የንግድ ማህበር ነዉ፥

34/“የክፍያ መፈፀሚያ ሰነድ አውጪ” ማለት በብሔራዊ ባንክ የክፍያ መፈፀሚያ ሰነድ እንዲያወጣ ፈቃድ የተሰጠዉ ኩባንያ ወይም በመንግስት ባለቤትነት የተያዘ ድርጅት ወይም ይሁንታ የተሰጠው ፣ ባንክ፣ አነስተኛ የፋይናንስ ተቋም ነዉ፥”

3/ የአዋጁ አንቀጽ 4 ንዑስ አንቀጽ(1) ፊደል ተራ( (ለ)፣ ተሰርዞ በሚከተለዉ አዲስ ፊደል ተራ( (ለ)ተተክቷል፥

"(ለ) የመንግስት ሰነዶች ማዕከላዊ የሰነደ ሙዓለ ነዋይ ግምጃ ቤት፤"

፬/ የአዋጁ አንቀጽ 4 ንዑስ አንቀጽ(2) ፊደል ተራ (ሀ) እና (መ)ተሰርዘዉ በሚከተለዉ አዲስ ፊደል ተራ (ሀ) እና (መ) ተተክተዋል፡

"ሀ) ለሚከተሉት ሰዎች ፈቃድ ወይም ይሁንታ የመስጠት

I. ለክፍያ ስርዓት ኦፕሬተር፣ እና

II. ለክፍያ መፈጸሚያ ሰነድ አውጪ፤

መ) ለተሳታፊዎች፣ ለክፍያ መፈጸሚያ ሰነድ አውጪዎችና የክፍያ ስርዓት ኦፕሬተሮች

I. የክፍያ ሥርዓት መሠረተ ልማቶችን ለመገንባትና እርስ በርሳቸውም ተናባቢ እንዲሆኑ ለማድረግ የሚያስፈልጋቸውን ኢንቨስትመንት፤

II. ወጪ ስለሚጋሩበት ሁኔታ

III. ለሚሰጡት አገልግሎት የሚያስከፍሉትን ክፍያ፤

IV. በኤሌክትሮኒክ ሂሳብ ዉስጥ የሚኖርን የገንዘብ ጣሪያ፣ በኤልክትሮኒክ ሂሳብ አማካኝነት ለሚፈጸም ግብይት፣ እና ከወኪል እና ከሌላ ኤሌክትሮኒክ መሳሪያ ወጪ የሚደረግን የጥሬ ገንዘብ ጣሪያን

በመመሪያ የመወሰን።"

5/ የአዋጁ አንቀጽ 5 ተሠርዞ በሚከተለዉ አዲስ አንቀጽ 5 ተተክቷል፡

<u>"5. ስለ ፈቃድ፣ ይሁንታ እና ክልከላ"</u>

"1/ ከብሔራዊ ባንክ በስተቀር ሌላ ማንኛውም ሰው ከባንኩ ፈቃድ ወይም ይሁንታ ሳያገኝ የክፍያ ሰነድ አውጪ ወይም ኦፕሬተር መሆን አይችልም"

2/ የኢትዮጵያ ፖስታ አገልግሎት ድርጅት በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 165/2002 ለሚያከናውነው የፋይናንስ አገልግሎት ተግባር በዚህ አዋጅ መሠረት ከኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ፈቃድ የማግኘትና ባንኩ በዚህ ረገድ ለሚያካሂዳቸው አስፈላጊ የቁጥጥርና ክትትል ሥራዎችም ተገዢ መሆን አለበት።

3/ ከብሔራዊ ባንክ በቅድሚያ የጽሁፍ ፈቃድ ካላገኘ በስተቀር ማናቸውም ኦፕሬተር ወይም የክፍያ ሰነድ አዉጪ፡-

(ሀ) አዲስ ስርዓት በስራ ላይ ማዋል ወይም አዲስ የክፍያ መፈጸሚያ ሰነዶችን ማውጣት፣

(ለ) ከሌላ ኦፕሬተር ጋር መዋሃድ ወይም የሌላ ሰው የክፍያ ሥርዓት ባለቤትነት መረከብ፤

(ሐ) በመቀላቀልም ሆነ በሌላ መንገድ የኦፕሬተሩን ሥራ መሸጥ ወይም ባለቤትነትን የሚያስቀሩ ማናቸውንም ዓይነት ስምምነቶች ወይም ውሎች መፈፀም ወይም በሥራ ዘርፉ ላይ ዓይነተኛ ለውጥ ማድረግ፤

(መ) አክሲዮኑን መልሶ መግዛት ወይም በመደበኛ ተግባሩ በተከሰተ ኪሣራ ምክንያት ካልሆነ በስተቀር ካፒታሉን መቀነስ፤

(ሠ) የመመስረቻ ጽሑፍ ማሻሻል፤ ወይም

(ረ) የክፍያ ስርዓቱን የሚያካሂድበትን የንግድ ስም መቀየር፤ አይችልም።

4/ ብሔራዊ ባንክ አንድ ኦፕሬተርን ስራውን ከማከናወን ወይም የክፍያ መፈጸሚያ ሰነድ አውጪን ሰነድ ከማውጣት የሚከተሉት ሁኔታዎች ሲኖሩ በጽሁፍ ሊከለክል ይችላል፤

(ሀ) አንድ የክፍያ ሥርዓት ወይም የክፍያ መፈጸሚያ መሳሪያ ለብሔራዊ የክፍያ ሥርዓቱ አስተማማኝነት፣ ደህንነት፣ ቀልጣፋነት እና ማሳለጥ ጎጂ ከሆነ፤ ወይም

(ለ) ክልከላው የሕዝብን ጥቅም ለማስጠበቅ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ፤

5/ የክፍያ ሰነደ አዉጪ ወይም የክፍያ ስርዓት ኦፕሬተር በማንኛዉም ጊዜ አግባብነት ያላቸዉን በወንጀል ድርጊት የተገኘ ገንዘብ ወይም ንብረት ህጋዊ አስመስሎ ማቅረብን እና ሽብረተኛን በገንዘብ መርዳትን ለመከላከል እና ለመቀጣጠር የወጡ የሀገሪቱን ህጎች ማክበር እና መተግበር ይኖርበታል።"

6/ የአዋጁ አንቀጽ 6 ተሠርዞ በሚከተለዉ አዲስ አንቀጽ 6 ተተክቷል፡

"<u>6. ፈቃድ ወይም ይሁንታ ለማግኘት ስለሚቀርብ ማመልከቻ</u>

1/ የክፍያ መፈጸሚያ ሰነድ አውጪ ወይም የክፍያ ስርዓት ኦፕሬተር ፈቃድ ለማግኘት ማመልከቻ ለብሔራዊ ባንክ ማቅረብ አለበት።"

"2/ ባንክ ወይም አነስተኛ የፋይናንስ ተቋም የክፍያ መፈጸሚያ ሰነድ ለማውጣት ይሁንታ ለማግኘት ማመልከቻ ለብሔራዊ ባንክ ማቅረብ አለበት።

3/ ከፋይናንስ ተቋም እና በመንግስት ባለቤትነት ከተያዘ ድርጅት ውጭ ያለ የንግድ ማህበር የክፍያ መፈጸሚያ ሰነድ አውጪ ወይም የክፍያ ስርዓት ኦፕሬተር ፈቃድ ማውጣት ከፈለገ ለዚሁ ዓላማ ብቻ የሚያገለግል ተቀጥላ ኩባንያ ማቋቋም አለበት።

4/ ብሔራዊ ባንክ ተቀጥላ ኩባንያ ስለሚቋቋምበት ሁኔታ በመመሪያ ሊወስን ይችላል ።

5/ በመንግስት ባለቤትነት የተያዘ ድርጅት በክፍያ መፈጸሚያ ሰነድ አውጪነት ወይም በክፍያ ስርዓት ኦፕሬተርነት ስራ ዘርፍ እንዲሰማራ የሚፈቅድ ልዩ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ሊኖረው ይገባል።

6/ ለክፍያ መፈጸሚያ ሰነድ አውጪነት እና ለክፍያ ስርዓት ኦፕሬተርነት ማመልከቻ የሚያቀርብ አመልካች በብሔራዊ ባንክ መመሪያ የሚወሰነውን ዝቅተኛውን የተከፈለ ካፒታል ማሟላት አለበት።

7/ የውጭ አገር ዜጎች በክፍያ መፈጸሚያ ሰነድ አውጪነት ወይም በክፍያ ስርዓት ኦፕሬተርነት ስራ ዘርፍ ሊሰማሩ ይችላሉ፤ ወይም በክፍያ መፈጸሚያ ሰነድ አውጪነት ወይም በክፍያ ስርዓት ኦፕሬተርነት ፈቃድ የሚሰጠውን ተቀጥላ ሊያቋቁሙ ይችላሉ።

8/ የውጭ አገር ዜጎችና ሙሉ በሙሉ በውጭ አገር ዜጎች ባለቤትነት የተያዙ ኢትዮጵያዊ ድርጅቶች  በክፍያ መፈጸሚያ ሰነድ አውጪነት ወይም በክፍያ ስርዓት ኦፕሬተርነት ስራ ዘርፍ የሚሰማሩት የሚፈለገዉ ካፒታል ሙሉ በሙሉ በዉጪ ምንዛሬ የተከፈለ ከሆነ ነው ።

9/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 8 የተገለጸው ቢኖርም በከፊል በውጭ አገር ዜጎች ባለቤትነት የተያዘ ኢትዮጵያዊ ድርጅት በክፍያ መፈጸሚያ ሰነድ አውጪነት ወይም በክፍያ ስርዓት ኦፕሬተርነት ስራ ዘርፍ የሚሰማራው የኩባንያዉን ካፒታል ብሔራዊ ባንክ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት በድርጅቱ በውጭ አገር ዜጎች የተያዘው ጠቅላላ ድርሻ በመቶኛ ተሰልቶ በውጭ ምንዛሪ የተከፈለ ከሆነ  ነው ።

10/ ብሔራዊ ባንክ ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል በውጭ አገር ዜጎች የተያዘ የክፍያ መፈጸሚያ ሰነድ አውጪ ወይም የክፍያ ስርዓት ኦፕሬተር ስራቸዉን በዉጭ ሀገር ዜጎች  ስለሚያሰሩበት፣ ስራቸዉን በዉጭ አካላት ስለሚያሰሩበት፣ እንዲሁም በእናት ኩባንያ እና በተቀጥላ መካከል ስለሚኖር ግንኙነት ሁኔታ በመመሪያ ሊወስን ይችላል።።

11/ የሥራ ፈቃድ ወይም ይሁንታ ለማግኘት የሚቀርብ አመልካች በብሔራዊ ባንክ መመሪያ የሚወሰነውን ክፍያ መክፈል አለበት።

12/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 11 የተደነገገዉ እንደተጠበቀ ሆኖ የዉጪ አገር ዜጎች በክፍያ ሰነድ አዉጪ ወይም በክፍያ ስርዓት ኦፕሬተር ስራ ዉስጥ ሲገቡ ብሔራዊ ባንክ በሚያወጣዉ መመሪያ መሰረት ተጨማሪ የኢንቨስትመንት ከለላ ክፍያን ሊያስከፍል ይችላል።

13/ ብሔራዊ ባንክ ማመልከቻው እንደደረሰው በጥያቄው ላይ መወሰን እንዲያስችለው አመልካቹ ስላቀረበው ዝርዝር መረጃ ትክክለኛነት፣ የክፍያ ሥርዓቱን ለማከናወን ስላለው ብቃት፣ የሥርዓቱ ተሳታፊዎች ስላቀረቧቸው የብቃት ማረጋገጫዎች፣ እንዲሁም ስለሌላ ማናቸውም ከማመልከቻው ጋር ስለተያያዘ ጉዳይ አስፈላጊ የመሰለውን ማጣራት ሊያደርግ ይችላል።

14/ ብሔራዊ ባንክ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ /13/ የተመለከተውን ማጣራት ካደረገ በኋላ የቀረበው ማመልከቻ የተሟላና የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎችና በባንኩ የወጡ መመሪያዎችን የተከተለ መሆኑን ሲያምንበት ከዚህ ቀጥሎ የተዘረዘሩትን ሁኔታዎች ግምት ውስጥ በማስገባት ለሥርዓቱ ፈቃድ ሊሰጥ ይችላል፦

(ሀ) ኦፕሬተሩ ወይም የክፍያ መፈጸሚያ ሰነድ አዉጪዉ ለማቋቋም ያቀደው ሥርዓት ወይም ለመስጠት ያቀደው አገልግሎት ተፈላጊነት፤

(ለ) የታቀደው ሥርዓት የቴክኒክ ደረጃና የአሠራር ንድፍ፤

(ሐ) የደህንነት መመሪያዎችን ጨምሮ የታቀደው ሥርዓት የሚመራባቸው ዝርዝር ሁኔታዎች፤

(መ) የሂሣብ ማጣራትና ማቻቻል ዝርዝር ሁኔታዎችን ጨምሮ በሥርዓቱ ገንዘብ የሚተላለፍበትን ሁኔታ፤

(ሠ) የአመልካቹ የፋይናንስ አቋም፣ የማስተዳደር ልምድ እና ታማኝነት፤

(ረ) የተገልጋዮች ጥቅም የሚከበርበትና አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ከኦፕሬተሩ ወይም ከክፍያ ሰነድ ዉጪ ጋር ያላቸው ግንኙነት የሚገዛበት ዝርዝር ሁኔታ፤

(ሰ) በገንዘብና ብድር ፖሊሲ ላይ ስለሚኖረው ፋይዳ፤ እና

(ሸ) ከብሔራዊ የክፍያ ሥርዓት ጋር በተያያዘ አግባብነት አላቸው ብሎ የሚያምንባቸውን ሌሎች ሁኔታዎች።

15/ ብሔራዊ ባንክ ከአመልካቹ የሚፈለጉ መረጃዎች ተሟልተው ከቀረቡበት ቀን ጀምሮ ባሉት 60 ቀናት ውስጥ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ /1/ መሠረት በቀረበ ማመልከቻ ላይ ውሳኔ ይሰጣል።

16/ ብሔራዊ ባንክ ፈቃድ ወይም ይሁንታ ለማግኘት የሚያመለክት ሰው ማቅረብ ያለበትን አስፈላጊ መረጃዎች እና ሌሎች አስፈላጊ ሁኔታዎችን በመመሪያ ሊወስን ይችላል።"

7/ በአዋጁ አንቀጽ 31 ቀጥሎ የሚከተሉት አዲስ አንቀጾች 32 እስከ 36 ተጨምረዉ ነባር አንቀጾች ከ32 እስከ 39 ከአንቀጽ 37 እስከ አንቀጽ 44 ሆነዉ ተሸጋሽገዋል፡

<u>"32. የክፍያ መፈጸሚያ ሰነድ አውጪ እና የክፍያ ስርዓት ኦፕሬተር ተግባራት"</u>

1/ በብሔራዊ ባንክ በጽሑፍ ሲጸድቅለት የክፍያ መፈጸሚያ ሰነድ አውጪ ኦቨርድራፍትን ጨምሮ አነስተኛ ብድር ፣ አነስተኛ ቁጠባ፣ አነስተኛ መድን፣ ወደ ሀገር የሚላክ አለምአቀፍ ሃዋላ

ወይም ሌላ ተዛማጅ አገልግሎት እንዲሰጥ ብሔራዊ ባንክ ፈቃድ ከሰጠዉ የፋይናንስ ተቋም ጋር በመሆን  በዲጅታል ዘዴ ማሳለጥ ይችላል።

2/ ብሔራዊ ባንክ በዚህ  አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተገለጹትን አገልግሎቶች ለመስጠት መሟላት ያለባቸውን ዝቅተኛ መስፈርት እና ቅድመ ሁኔታ በመመሪያ ሊወስን ይችላል።

33. <u>ድንበር ተሻጋሪ ክፍያዎች</u>

1/ ከብሔራዊ ባንክ በቀር ማንኛውም ሰው ድንበር ተሻጋሪ ክፍያዎችን ለማስተላለፍ፣ ለማጣራት፣ ለመክፈል፣ ለመሳተፍ፣ እና ለማስተዳደር የሚያስችል የኦፕሬሽን ወይም የስርዓት መዋቅር ውስጥ ያለብሔራዊ ባንክ ይሁንታ መግባት አይችልም።

2/ ድንበር ተሻጋሪ ክፍያዎችን ከማስተላለፍ፣ ከማጣራት፣ ከመክፈል፣ ከመሳተፍ፣ እና ከማስተዳደር ጋር በተያያዘ የሚነሱ ጉዳዮችን በተመለከተ ብሔራዊ ባንክ መመሪያ ሊያወጣ ይችላል።

34. <u>ከሀገር ዉስጥ፣ ቀጠናዊ እና ዓለም-አቀፋዊ ተቆጣጣሪ ተቋማት ጋር ስለመተባበርና በጋራ ስለመስራት</u>

ብሔራዊ ባንክ መረጃ ለመለዋወጥ እና በብሔራዊ የክፍያ ስርዓቱ ላይ የተቀናጀ  ክትትል ለማድረግ ብሎም የብሔራዊ ክፍያ ስርዓቱን አስተማማኝነትና ውጤታማነት ለማረጋገጥ ከአገር ውስጥ፣ ከቀጠናዊ እና ዓለም-አቀፋዊ የቁጥጥር አካላት ጋር በጋራ ሊሰራ ይችላል። እንደዚህ ዓይነቱ የጋራ አሰራር ምስጢራዊ መረጃዎች የሚጠበቁበትን ሁኔታ ማካተት አለበት።

35. <u>ዓለም-አቀፍ የክፍያ ስርዓት መርሆችንና እስታንዳርዶችን የራስ አድርጎ ስለመደንገግ</u>

ብሔራዊ ባንክ የብሔራዊ የክፍያ ስርዓቱን ደህንነት፣ውጤታማነትና አስተማማኝነት ለማረጋገጥ ለክፍያ ስርዓት ተገቢነት ያላቸውን ዓለም-አቀፍ መርሆችንና እስታንዳርዶችን በመመሪያ የራሱ አድርጎ ሊደነግግ ይችላል።"

36. <u>**ተፈጻሚ ድንጋጌዎች**</u>

የአዋጁ አንቀጽ  7፣8፣9፣11፣18 እና 26 ድንጋጌዎች እንደነገሩ ሁኔታ ለክፍያ ፈጸሚያ ሰነድ አውጪ ተፈጻሚ ይሆናሉ።

**3. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ**

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

**አዲስ አበባ ……../……….. 2014 ዓ.ም**

**ሣህለወርቅ ዘውዴ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**